# <u>ብቻዬን ቀርቼ</u>

እንዲያው ሳይቸግረኝ ፤ ድንገት ተሳስቼ

በግል ፍላጎት ፤ ጥቅም ተመርቼ

ውስጡን ሳልመረምር ፤ ላዩን ብቻ . . አይቼ

ባገር የተጠላ ፤ ባንዳ ተጠግቼ

አይንሽ ላፈር . . አሉኝ ፤ ወዳጅ ዘመዶቼ ።

መካሪ ሲመክረኝ ፤ ብቀበል ሰምቼ

አሻፈረኝ ባልል ፤ በዕብሪት ተሞልቼ

አላዝንም ነበረ ፤ ከማጥ ውስጥ ገብቼ

ልቤን ለማይረባ ፤ ከሃዲ ሰጥቼ ።

አገር አሳዘኜ ፤ ስህተት ሰርቼ

የተጠቀምኩ መስሎኝ ፤ በድብቅ ዶልቼ

ይቅርታም ሳልጠይቅ ፤ ጥፋትም አጥፍቼ

ይኸው . . ዳር ቀረሁኝ ፤ ወጣሁ ተገፍቼ

ከወያኔም ሳልሆን ፤ ወይ ከወገኖቼ ።

መደበቂያ ባገኝ ፤ መሄጂያ ጠፍቼ

የማልታይበት ፤ ከሰዎች ሸሽቼ

ፈረንጅ አገር ሄጂም ፤ እርቄ ወጥቼ

አዩኝ . .አላዩኝ ስል ፤ ሁልጊዜ ሰግቼ

አደጅም አልወጣ ፤ መቼ ስራ አጥቼ

ጦር ሆኖ እየታየኝ ፤ የሰው አይን ፈርቼ

የምላወስበት ፤ መተንፈሻ አጥቼ

ከመቃብር በላይ ፤ የቁም . . ሞትን ሞቼ

መኖር ግድ ሆነብኝ ፤ አንገቴን ደፍቼ

እኔም . . እንደ ባንዳ ፤ በሰው ተጠልቼ

እወዘወዛለሁ ፤ ብቻዬን ቀርቼ ።

ታዛቢው ... March, 12, 2010